# የአቡኑ ገዳም



ተራራ ወጥቼ፣ ከአቡኑ ዘንድ ሄጄ መስቀል ለመሳለም
አስቤ ነበረ
ክረምቱ በረታ፣ ምንም አልተቻለ፣ ያሰብኩት ሳይሞላ፣
ሳይሆንልኝ ቀረ
ዳመናው ዝናቡ፣ ጉምና ጭጋጉ፣ ይህ የዛሬ ክረምት
መች ያነቃንቃል!
ደጁን አጨቀይቶት፣ ወንዙም ጉርፍ ሞልቶት፣ አጅጉን
አስፈሪ፣ በጣም ያስጨንቃል
በታምር በፀሎት፣ ከተራራው አፋፍ፣ ከዳመናው በላይ
የገደሙት ገዳም
ደካማው ጉልበቴ፣ እንደምን ይቻለው፣ ጭቃውን ሽርተቴ፣ የኖሁን ዝናም
ዛሬ፣ ነገ እያልኩ ሰማዩና ምድሩን ሳስስ ስመለከት፣ ስቃኝ አድማሱን
ዓይኖቼም ደከሙ፣ አለቀ ጉልበቴ፣ መቃብር ቁፋሮ፣ ሰርክ መማሱን!
ማለዳ-ማለዳ ደረትዋን ገልብጣ፣ ድምጿንም ከፍ አደርጋ የምትጮኸው ወፍ
እየቀሰቀሰች እንቅልፍ ነሳችኝ፣ ሽፍንፍን ብዬ፣ ተኝቼ በሰላም በደህና እንዳላርፍ!
ምድር-ዓለሙ ክዶኝ፣ ሁሉም ጥሎኝ ሄዷል፣ ጠያቂም የለኝም ከቶ ሚያጽናናኝ
ወፊቱስ የት ሄደች? ከጠፋች ቆይታለች፣ ድምጿንም አልሰማሁ፣ እንዳታዝናናኝ...
ደጋግሞ እየቀየ የሚነፍሰው ነፋስ አለው መጥፎ ጠባይ፣ ኃይለኛ አዙሪት
የጐጆየን ክዳን በትኖ እያነሳ፣ ምን ዓይነት ተንኮል ነው፣ ምን ዓይነት ዕብሪት!
መቸ ይኸ ብቻ! ሰማዩን ተርትሮ አስደንጋጭ ብልጭታ መብረቅ ሲፈነጥቅ
አከታትሎ ይሏል የሰማይ ነጐድጓድ ቤቱን አንቀጥቅጦ ጆሮ እስኪሰነጥቅ
ተራራ አልወጣህ፣ ታቡን ዘንድ አልደረስክ፣ መስቀል አልተሳለምክ ብሎ ነው መሰለኝ
ከዚያ ላይ ስወጣ ገደል ከምገባ፣ ወድቄ ከምሞት፣ ወይም አንሸራትቶኝ ከሚሰባብረኝ
ከዚሁ ከቤቴ ካልጋዬ ተኝቼ፣ በንፋስ፣ በመብረቅ ነጉዶ አንጐዳጉዶ እንዳሻው ያድርገኝ!





ገ/ኢ.. ጐርፉ።